# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን በሚማሩበት ጊዜ የትኞቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ አብዝተው እንደሚጠቀሙ መለየት

(በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝም የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በ ያሲን አደም

ሀምሌ 2015 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን በሚማሩበት ጊዜ የትኞቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ አዘውትረው እንደሚጠቀሙ መመርመር ነው፡፡ ተሳታፊዎች በኦሮሚያ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በሩፍሴ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በመማር ላይ ያሉ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአመች ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ጥናቱም ገላጭ የምርምር ስልትን የተከተለ ነው፡፡ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ አማካኝነት የጥናቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎችም በአይነታዊና መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልቶች ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን በሚማሩበት ጊዜ ጥቅል አካካሽ ብልሃቶችን 101(144.3%) ያህልጊዜ በመደጋገም ሲጠቀሙ፣ ሌሎቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ አዘውተረው እንደማይጠቀሙባቸው አመላክቷል፡፡ ለዚህ ተግባር እንደምክናየት የቀረቡት የተማሪዎቹ የትውስታ፣ የአዕምሮታዊ፣ የልዕለ አዕምሮታዊ፣ስሜትነክና ማህበራዊ ብልሃቶችን ሲገለገሉ ሁልጊዜ እንደማይጠቀሙበት ሲያሳየን በአንጻሩ ደግሞ የአካካሽ ብልሃት አጠቃቀማቸው በብቃት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም በመነሳት ተጠኚ ተማሪዎች በተደጋጋሚ አብዝተው የሚጠቀሙት አካካሽ ብልሃቶችን ሲሆን ሌሎቹን ብልሃቶች ግን አዘውትረው እንደማይጠቀሙባቸው ከሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሐፍት አዘጋጆች የቃላት መማር ብልሃቶችን በተመለከተ ስነ-ዘዴዎችን ቀርጸው እንደ አንድ የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴ ቢጠቀሙበት፣ የቋንቋ መምህራን ተማሪዎችን በራሳቸው ጥረት እንዲሳተፉ ቃላትን የመማር መንገድ ቢያመቻቹላቸውና ክትትል ቢያደርጉላቸው የሚሉ የመፍትሄ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በመማር ማስተማሩ ሂደት በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ በሚደረጉ መስተጋብሮች ተግባቦቱ የቀለጠፈና የዳበረ ይሆን ዘንድ የቃላት እውቀት የጎላ ሚና አለው፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር በዋናነት ለቃላት ትኩረት መሰጠት አለበት፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በተግባቦት ሂደት ልምዳቸውን፣አላማቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ድርጊታቸውንና ሐሳባቸውን በተመለከተ የታቀደውን መልዕክት በተገቢው መንገድ ለሌሎች ለማስተላለፍም ሆነ ለመቀበል የቃላት እውቀታቸው ቁልፍ ሚና አለው (McCrostie, 2007; Read, 2000; Nation, 2001)፡፡ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋቸው ራሳቸውን ለመግለፅ ፈልገው መግለጫ ቃላት ሲያጡ በተግባቦት ሂደት የሚያሣድርባቸው የፍርሃት ስሜት ከፍተኛ መሆኑንና በቋንቋው ላይ አሉታዊ አመለካከት እንደሚያሳድርባቸው በመግለጽ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት እውቀት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው Nyikos &Fan(2007) ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩም Atkins እና ሌሎች (1995:199) እንደሚሉት ብዙዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በተተኳሪው ቋንቋ የመጠቀም ሰፊ ዕድል የላቸውም፡፡ በቋንቋው የሚጠቀሙት በመማርያ ክፍል ውስጥ በሚማሩበት ወቅት ላይ የተወሰነ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪዎቹ ቋንቋውን ለተለያዩ ጉዳዮቻቸው ሲጠቀሙ በጣም ይቸገራሉ፡፡ በዚህ በጣም ውስን በሆነ አጋጣሚ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርታቸውን ውጤታማ ለማድረግ በራሳቸው ጥረት ቋንቋውን መማራቸው ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ለትምህርታቸው ኃላፊነትን ወስደው በመማርያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በተለያዩ መንገዶች ራሳቸውን ለመርዳት መነሳሳት አለባቸው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክናየት

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት እንዲካሄድ መነሻ የሆኑት ችግሮች መካከል አጥኚው ለረጅም አመታት ባካበተው ልምድ መሰረት ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገቡ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የቃላት አጠቃቀም ብቃታቸው አናሳ በመሆኑ በማመንና በቃላት ብልሃት አጠቃቀማቸው መካከል ተጣጥሞነት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር እንዲሁም የቃላት ብልሃቶችን በመገልገል በቋንቋ ችሎታቸው ላይ ልዩነት ያሳያሉ ወይስ አያሳዩም የሚሉትን ለመጠቆም ተነሳስቷል፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን በሚማሩበት ጊዜ የትኞቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ አብዝተው እንደሚጠቀሙ መለየት ነው።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል። የዚህን የጥናት ውጤት መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን በመማር ሂደት አጋዥ የሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን መርጠው እንዲጠቀሙ ያበረታታቸዋል። የቃላት መማር ብልሃቶችን መጠቀም በተማሪዎች ውጤት ላይ ያለውን ፋይዳ የትምህርተ ባለሙያዎች ተረድተው በስርዓተ ትምህርት ወቅት ብልሃቶችን ቢያካትቱ ተማሪዎቹ በተለያየ መንገድ እንዲማሩ ያግዛቸዋል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

በኦሮሚያ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በደዋ ጨፋ ወረዳ ከሚገኙ አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪ ሆኗል። ጥናቱ በ2015 ዓ.ም  በአስረኛ ክፍል በመማር ላይ ከሚገኙ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ በፈቱ ከሁለት መማርያ ክፍል ተማሪዎች በመውሰድ ብቻ ነው። ጥናቱ በመማር ማስተማር ዙርያ የሚገኙትን ችግሮች ሁሉ የሚዳስስ ሳይሆን አፋቸውን በኦሮሞኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቃላትን መማር ብልሃቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው።

በወረዳው ያሉ አራቱንም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማካተት ቢቻል የተሻለ እንደሚሆን አጥኚው ያምናል። ነገርግን ከሚወስደው ጊዜ፣ ጉልበትና ወጭ የተነሳ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች ማካተት አልተቻለም።

# 2. ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቃላት መማር ብልሃቶች ምንነት

*የቃላት መማር ብልሃቶችን አስመልክተው የተለያዩ ተመራማሪዎች በተለያየ መንገድ ቢተረጉሙትም በጽንሰሀሳብ ደረጃ ተመሳሳይነትና ወጥ የሆነ ትርጉም እንደሌለው ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ለአብነት ያህል Catalon (2003) እንደገለጹት የቃላት መማር ብልሃቶች የእንግዳ ቃላትን ትርጉምና የታወቁ ቃላትን ፍቺ ለመለየት፣ በረጅም ጊዜ ትውስታ በመፍጠርና በሚያስፈልግ ጊዜ አስታውሶ በአዳምጦ መረዳት፣ በአንብቦ መረዳት፣ በንግግርና በጽሁፍ ጊዜ አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችሉ ብልሃቶች ናቸው፡፡*

*የቃላት መማር ብልሃቶች ተማሪዎች ለእንግዳ ቃላት ሲጋለጡ የቃላቱን ትርጉም ለመገንዘብና ቃላቱን በዘውታሪነት በአእምሯቸው ውስጥ ስርጾ እንዲቀር የሚገለገሉባቸው የራሳቸው መለያ ባህርያት ናቸው* Jurkovic (2006)፡፡

## 2.2 የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል

*ቃላትን የመማር ብልሃቶች አከፋፈል አንድ ወጥ መንገድ የተከተለ አይደለም፡፡ ምሁራኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን የከፋፈሏቸው በተለያየ መንገድ ነው፡፡ ካሉት አከፋፈሎች ይህ የ*Oxford (1990) አከፋፈል የተሻለና በሌሉች ጥናቶች የቀረቡ የመማር ብልሃቶችን አካቶ የያዘ በምሳሌዎች አሰደግፎ የሚያቀርብ መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ከተሰጡት ምክናየቶች መካከልም ዝርዝር ብልሃቶችን በተዋረድ በማስቀመጥ በሁለት አብያት ክፍሎች ብቻ በመክፈልና በስሩም ንዑሳን ክፍሎችን በመዘርዘር፣በማብራራት ለመረዳት ቀላል መሆኑን ተመራጭ ያደርገዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በ Oxford(1990) የቀረበውን አከፋፈል መሰረት በማድረግ ነው፡፡

### 2.2.1 ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች

እንደ Oxford (1990፣37) አገላለጽ ተማሪዎች በግልጽ የታላሚውን ቋንቋ በትምህርቱ ሂደት እየተወያዩ የተለያዩ ተግባራትን እየሰሩ የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት እንዲለማመዱና እንዲማሩ በቀጥታ የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ በቀጥተኛ ብልሃቶች ስር የሚካተቱ ዋና ዋና ንዑስ ብልሃቶችም የትውስታ ብልሃቶች፣ አእምሯዊ ብልሃቶችና አካካሽ ብልሃቶች ናቸው፡፡ የትውስታ ብልሃቶች ተማሪው ቃላትን በአእምሮው መዝግቦ በመያዝና የረጅም ጊዜ ትውስታ በመፍጠር በአስፈላጊው ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም የሚያግዙ ብልሃቶች ናቸው፡፡በዚህ ብልሃት ስር ማቧደን፣

ስዕል መፍጠር፣ ማያያዝ፣ በትውስታ ውስጥ ድምጽን መወከል፣ ክለሳ ማካሄድ በሚል ተካተው ይገኛሉ፡፡

አዕምሯዊ ብልሃቶች ተማሪው የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት በግልጽ አእምሮውን በመጠቀም ተገንዝቦና ከራሱም አፍልቆ በመለማመድ እንዲማር የሚያስችሉት ብልሃቶች ናቸው፡፡ በዚህ ብልሃት ስር መተርጎም፣ ምንጭ መጠቀም፣ ማሸጋገር፣ ድግመቅንብር፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ወዘተ. ተካተው ይገኛሉ፡፡ አካካሽ ብልሃቶች ተማሪው የቋንቋ እጥረት ሲያጋጥመው ምትክ ይሆናሉ ብለው የሚጠቀሙባቸውን በሙሉ የሚያካትቱ ናቸው፡፡

## 2.2.2 ኢ-ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች

ኢ-ቀጥተኛ ብልሃቶች በማቀድ፣ በመገምገም ጭንቀትን በቁጥጥር ስር በማድረግ፣ ወዘተ. ቋንቋን መማር ቀጥተኛ ያልሆነ ድጋፍ የሚሰጡትን ብልሃቶች የሚያካትቱ ናቸው፡፡ በኢ-ቀጥተኛ ቃላት የመማር ብልሃቶች ስር የሚካተቱ የመጀመርያው ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ሲሆን ተማሪው ትምህርቱን በዕቅድ ለመምራት፣ የትምህርቱን አካሄድና አሰራሩን ለመከታተል፣በአጠቃላይ ያሳየውን ለውጥና የትምህርቱን ውጤት ለመገምገም የሚጠቀምባቸው ብልሃቶች ናቸው (Oxford, 1990)፡፡

ስሜትነክ ብልሃቶች ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሚያድርበትን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት እንዲሁም አሉታዊ ዝንባሌ ለመቋቋም (ለመቆጣጠር) የሚጠቀማቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ ማህበራዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ቃላትን ሲማሩ ከአካባቢውና አብረው ከሚኖሩት ማህበረሰብ ጋር በመገናኘት ፣በመግባባት፣ በመተባበርና በመስራት ፣ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በመጠየቅ ፣ ራሳቸውን በራሳቸው በማበረታታት ቋንቋውን የሚማሩበት ብልሃት ነው፡፡

## 2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በላይነሽ (2002) "በኦሮሚያ ክልል የመቱ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶች ፍተሻ"በሚል ርዕስ ሲሆን የጥናቱም ውጤት ተጠኚዎቹ ቃላትን ሚማሩ ቃላትን የመማር ብልሃት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ምንም እንኳ በርዕሱ ቢመሳሰልም ከተጠኚዎች ብዛት፣ ከትኩረት አቅጣጫ፣ከአላማና ከቦታ አኳያ ይህ ጥናት ይለያል፡፡

# 3 የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን በሚገለገሉበት ጊዜ የትኞቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ለመለየት ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ገላጭ የምርምር ዘዴን መርጧል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በ2015 ዓ.ም በደዋ ጨፋ ወረዳ ውስጥ ባሉ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በአመቺ ናሙና አመራረጥ ዘዴ የሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በጥናቱ ተመርጧል፡፡ ምክናየቱም የተመረጠው ትምህርትቤት ለገጠሩ ኗሪ አማካኝ ቦታ ላይ የተሰራ በመሆኑና በብዛት የኦሮምኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚማሩበት ስለሆነ ነው፡፡

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የአስረኛ ክፍል በአላማ ተኮር የንምና ዘዴ ተመርጧል፡፡ አስረኛ ክፍል የተመረጠበት ምክናየት የክፍል ደረጃው አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ አማካይ ላይ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ላይ ያለውን የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀም እና የተግባቦት ሁኔታቸውን በጥልቀት በማየትና በማሰብ ነው፡፡

### 3.2.3 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በ2015 ዓ.ም በመደበኛነት በ10ኛ ክፍል ተመዝግበው ከሚማሩ ተማሪዎችና የሚማሩበትን ምድቦች ብዛት መሠረት በማድረግ ከአራቱም ምድቦች በኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን በሁለት መማሪያ ክፍል ተለይተው የሚመሩትን በመለየት ሰባ ተማሪዎችን በአመቺ ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱ ተሳታፊ ከሆኑት ተማሪዎች የሚሰበሰቡት መረጃዎች አስተማማኝ ይሆኑ ዘንድ የሚከተሉት የመረጃ መሰብቢያ መሳሪያዎች (የጽሁፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ በአጋዥነት) አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ በተግባር ላይ ውለዋል፡፡

### 3.3.1 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ በOxford(1990) የቃላት መማር ብልሃቶችን መሰረት ያደረጉ 30 ጥያቄዎችን ለዚህ ጥናት በሚያመች መልኩ ተሻሽለው የተወሰዱ ሲሆን መጠይቁ ለተተኳሪ ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና አንድ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህር እንዲገመግሙት ተደርጓል፡፡በመጠይቁ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃታቸውን የሚጠይቁ የትውስታ፣የአዕምሮታዊ፣ የአካካሽ፣የልዕለአዕምሮታዊ፣የስሜትነክ ቁጥጥርና ማህበራዊ ብልሃቶችን አካቶ መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል ነው፡፡

### 3.3.2 ቃለመጠይቅ

የዚህ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አላማ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ቃላትን በሚማሩበት ጊዜ የትኞቹን የቃላት መማር ብልሃቶች እንደሚጠቀሙ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ሲሆን ከሁለት የመማርያ ክፍል ውስጥ ነሲብ ናሙናን በመጠቀም 14ተማሪዎችን በመምረጥ የጥናቱ አላማ ከተብራራላቸው በኃላ ለቀረበላቸው አስር ጥያቄዎች የሚያውቁትን መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

# 4 የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮሚያ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በደዋ ጨፋ ወረዳ በሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የትኞቹን የቃላት መማር ብልሃቶች አዘውትረው እንደሚጠቀሙ መለየት ሲሆን በዋናነት በቀጥተኛና በኢ-ቀጥተኛ የቃላት መማር ብልሃቶች ስር የትኞቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ እንደሚጠቀሙ ለመተንተን ነው።

**ሰንጠረዥ1፡-** በቀጥተኛ የቃላት መማር ብልሃት ስር የተጠቀሚቸው ጥቅል ብልሃቶች

| ተ/ቁ | ጥቅል ብልሃቶች | የተሰጡ ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድጊዜ | | አልፎአልፎ | | በጭረሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | ጥቅል የትውስታ ብልሃቶች አጠቃቀም | 57 | 81.4% | 84 | 119.9% | 177 | 252.9% | 101 | 145.6% |
| 2 | ጥቅል አዕምሮታዊ ብልሃቶች | 118 | 141.3% | 155 | 221.3% | 425 | 607% | 72 | 102.5% |
| 3 | ጥቅል አካካሽ ብልሃቶች | 101 | 144.3% | 62 | 88.5% | 28 | 39.8% | 19 | 27.1% |

ጥያቄ1.ተማሪዎች ቃላትን ሲማሩ አዳዲስ መረጃዎችን ለማስታወስ የሚያገለግሉ ጥቅል የትውስታ ብልሃቶችን ደጋግመው እንደሚጠቀሙ ተጠይቀው177 (252.9%) ያህልጊዜ ብልሃቱን አልፎአልፎ ሲጠቀሙ፣101 (145.6%) ጊዜ ደግሞ በመደጋገም በጭራሽ እንደማያስታውሱ ምላሽ ሰጥተዋል። በአንጻሩ 84(119.9%) ያህል ጊዜ አንዳንድ ጊዜ ደጋግመው ሲጠቀሙ፣57 (81.4%) ያህል ጊዜ ደግሞ አዳዲስ መረጃዎችን ሁልጊዜ በመደጋገም የትውስታ ብልሃቶችን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል።

ጥያቄ2. ኢ-አፍፈት ተማሪዎች አዕምሮን በመጠቀም ተረድተውና ከራስ አፍልቀው ደጋግመው በመለማመድ እንዲማሩ የሚያስችል ጥቅል አዕምሮታዊ ብልሃቶችን ተጠይቀው 425(607%) ያህልጊዜ በመደጋገም አልፎአልፎ እንደሚጠቀሙበት ሲገልጹ፣155(221.3%) ጊዜ ደግሞ ጥቅል ብልሃቶችን አንዳንድ ጊዜ እንደሚገለገሉ ያሳያል። በአንጻሩ ደግሞ118 (141.3%) ያህልጊዜ

በመደጋገም ሁልጊዜ ብልሃቱን እንደሚጠቀሙ ሲያሳዩ፣ 72(102.5%) ጊዜ ደጋግመው በጭራሽ እንደማይጠቀሙበት በሰንጠረዥ1 ለመረዳት ተችሏል፡፡

ጥያቄ 3. ተማሪዎች የቃላት እውቀት ክምችት እጥረት ሲያጋጥማቸው ጥቅል አካከሽ ብልሃቶችን ደጋግመው መጠቀምና አለመጠቀማቸውን ተጠይቀው 101(144.3%) ጊዜ በመደጋገም ሁልጊዜ በማካካስ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 62(88.5%) ያህልጊዜ ደግሞ አካካሽ ብልሃቶችን አንዳንድ ጊዜ እየደጋገሙ እንደሚጠቀሙ ያሳየል፡፡ በአንጻሩ 28(39.8%)ያህልጊዜ ደጋግመው አልፎአልፎ አንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣19(27.1%)ያህልጊዜበመደጋገም ደግሞ ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይጠቀሙበት ከትንተናው መረዳት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ለ14 ተማሪዎች አካካሽ ብልሃቶችን የሚመለከቱ ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸው አብዛኞቹ አስር ተማሪዎች አዘውትረው በመደጋገም እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡

ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ1 ከተገለጹት ጥቅል ብልሃቶች ለመረዳት እንደተቻለው አብዛኞቹ ተጠኚ ተማሪዎች አዘውትረው በተደጋጋሚ የሚጠቀሙት አካካሽ ብልሃቶችን ሲሆን ሌሎቹን የትውስታና የአዕምሮታዊ ጥቅል ብልሃቶችን አዘውትረው እንደማይጠቀሙባቸው የትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡

**ሰንጠረዥ2፡-** በኢ-ቀጥተኛ የቃላት መማር ብልሃት ስር የተጠቀሟቸው ጥቅል ብልሃቶች

| ተ/ቁ | ጥቅል ብልሃቶች | የተሰጡ ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድጊዜ | | አልፎአልፎ | | በጭረሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 4 | ጥቅል ልዕለአዕምሮታዊ ብልሃቶች አጠቃቀም | 19 | 27% | 44 | 62.8% | 122 | 174.2% | 95 | 135.6% |
| 5 | ጥቅል ስሜትነክ ብልሃቶች | 38 | 54.5% | 78 | 111.3% | 144 | 205.5% | 20 | 28.5% |
| 6 | ጥቅል ማህበራዊ ብልሃቶች | 21 | 30% | 46 | 65.7% | 61 | 87.1% | 12 | 17.1% |

ጥያቄ 4. ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥማቸው ጥቅል ልዕለአዕምሮታዊ ብልሃቶችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለመፈተሽ ጥያቄ ቀርቦላቸው አብዛኞቹ 122(174.2%) ያህልጊዜ በመደጋገም አልፎአልፎ ብልሃቶቹን እንደሚጠቀሙበት ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡

ጥያቄ 5. በቃላት መማር ሂደት የተማሪዎችን ስሜት ለመቆጣጠር የሚረዱጥቅል ስሜትነክ ብልሃቶች ቀርበውላቸው አብዛኞቹ 144(205.5%) ያህል ጊዜ በመደጋገም አልፎ አልፎ ጥቅል ብልሃቶቹን እንደሚጠቀሙበት ከመረጃው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ጥያቄ 6. ተጠኚ ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ቃላትን እንዲማሩ የሚረዱ ጥቅል ማህበራዊ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ተጠይቀው ነበር፡፡ ከላይ ከሰንጠረዥ2 እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ 61(87.1%) ያህል ጊዜ በመደጋገም አልፎ አልፎ ብልሃቱን እንደሚጠቀሙበት መረጃው ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደተቻለው የተጠኚ ተማሪዎች የቃላት ብልሃት አጠቃቀም አነስተኛ እንደሆነና ከአካካሽ ብልሃቶች ውጭ ሌሎቹን ጥቅል ብልሃቶች በተደጋጋሚ አዘውትረው እንደማይጠቀሙ ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡

# 5. ማጠቃለያ፣መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በአማራ ክልል በኦሮሚያ ብሔረሰብ ልዩዞን በደዋ ጨፋ ወረዳ በሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የትኞቹን የቃላት መማር ብልሃቶች ደጋግመው እንደሚጠቀሙ መለየት የሚል ዋና አላማ መሰረት አድርጎ የተጠና ነው፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ የሚከተለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

- ኢ-አፍፈት ተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ በተደጋጋሚ የሚገለገሉባቸው አካካሽ ብልሃቶችን ሲሆን ሌሎቹን ብልሃቶች ግን በተደጋጋሚ አዘውትረው እንደማይጠቀሙባቸው ማደማደም ተችሏል፡፡

## 5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች

የዚህን ጥናት ግኝት ተግባራዊ ለማድረግና የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃት ለማሻሻል የሚከተሉት መፍትሄዎች ተሰንዝረዋል፡፡

- የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሐፍና የመምህር መምርያ አዘጋጆች የቃላት ትምህርትን ሲያዘጋጁ የቃላት መማር ብልሃቶችን የተመለከተ ስነ-ዘዴ ቀርጸው እንደ አንድ የትምህርት ማስተላለፊያ መንገድ ተጠቅመው በግልጽ ለመለማመድ የሚረዳ አድርገው ቢያዘጋጁት፣

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የቃላት እውቀት ለማሻሻል አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት እንዲሳተፉ ሁልጊዜ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ቢያመቻቹላቸውና ክትትል ቢያደርጉ፣

## ዋቢ መጻሕፍት


በላይነሽ ደነቀ፡፡ (2002)፡፡ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን የመማር ብልሃቶች ፍተሻ፡፡" የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

Atkins, J.et.al. (1995). Skills Development Methodology፡ Part I. Addis Ababa: Addis Ababa University Printing Press.

Catalon, R, M. J. (2003). Sex Differences in L2 Vocabulary Learning Strategies፡ International Journal of Applied Linguistics, 13(1), 54-77.

Jurkovic, V. (2006). Vocabulary Learning Strategies in an ESP Context፡ TESOL Quarterly, 2(1), 23-32.

McCrostie, J. (2007). Examining Learner Vocabulary Note Books፡ ELT Journal,61(3), 24.

Nation, P. (2001). Learning Vocabulary in another Language: Cambridge: Cambridge University Press.

Nyikos, M. and Fan, M. (2007). Areviow of Research on Vocabulary Learning Strategies In A. Cohen and Macaro (Eds.), Language Learner Strategies (pp.251-273). Oxford: Oxford University Press.

Oxford, R. (1990). Language Learning's Strategies: What Every Teacher Should Know. New York: Newburg House Publishers.

Read, J. (2000). Assessing Vocabulary; Cambridge: Cambridge University Press.